**Español:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_spanish.pdf
**Kreyòl ayisyen:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_hcreole.pdf
**বাংলা:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_bangla.pdf
**አማርኛ:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_amharic.pdf
masspowerchoice.com/cambridge/letter_arabic.pdf **:عربى**

# የካምብሪጅ ከተማ

## የማሕበረሰብ የሙብራት/ኤሌክትሪክ ቅንብር ፕሮግራም (COMMUNITY ELECTRICITY AGGREGATION PROGRAM)

## የማስታወቅያ ደብዳቤ

ነሃሴ (August) 24 ቀን 2023

የተከበራችሁ የካምብሪጅ ነዋሪዎች ወይም የንግድ ስራ ባለቤቶች፡

ይህ ደብዳቤ የኤሌክትሪክ ክፍያዎን በተመለከተ አስፈላጊ መረጃ የያዘ ነው።

በአሁኑ ወቅት ፡ ኤቨርሶርስ ቤዚክ አገልግሎት (Eversource Basic Service) በሚባል የሙብራት/የኤሌክትሪክ አገልግሎት ነው በመገልገል ላይ የሚገኙት:: ይህም ማለት የሙብራት/ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያገኙት ኤቨርሶርስ((Eversource) ከሚባለው የኤሌክትሪክ ተቋም ነው:: ይሄው ተቋም ሙብራት እንዲደርሶት ያደርጋል:: አሱም ነው ሙብራት ወይም ኤሌትሪክ ከሌሎች የሚገዛሎት ማለት ነው::

ይሁንና የካምብሪጅ ከተማ፤ የካምብሪጅ ማህበረሰብ ኤሌክትሪክ (Cambridge Community Electricity-ሲ-ሲ-ኢ-CCE) የሚባል ፕሮግራም አለው። በዚህ ፕሮግራም ኤቨርሶርስ (Eversource) ኤሌክትሪክ ያቀርብሎታል፣ ከተማው ግን የራሱን የኤሌክትሪክ አቅራቢ ይመርጣል። ከተማው ይህንን ፕሮግራም ከጸሃይ የሚመነጭ አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል በካምብሪጅ ለመፍጠር ይጠቀምበታል። የእርሶ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ፤ አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲጨመር ያግዛሉ ማለት ነው።

**ይህንን ደብዳቤ ካገኙ በኋላ ምንም መልስ ካልሰጡ፤ በኦቶማቲክ መንገድ በካምብሪጅ የማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) ውስጥ ይገባሉ።**

**በኦቶማቲክ መንገድ ወደ ፕሮግራሙ ከመግባት ለመዳን፤ በፕሮግራሙ መመዝገብ አልፈልግም የሚል ጥያቄዎን ያዘለው ፖስታ ከመስከረም (September) 26 ቀን 2023 በፊት ፖስታ ቤት እንደገባ የሚያሳይ ምልክት ሊኖረው ይገባል፡፡**

**የሚሳተፉባቸው መንገዶች፡** ኤቨርሶርስ (Eversource) የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ መሆኑን ይቀጥላል። የኤሌክትሪክ ክፍያዎን መክፈል የሚቀጥሉት ኤቨርሶርስ (Eversource) ነው፤ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ቢቋረጥቦት የሚደውሉትም እነሱ ጋ ነው። ከኤቨርሶርስ (Eversource) በሚደርሶት የክፍያ ወረቀት ላይ ግን ኤሌክትሪክ የሚያቀብሎት ዳይሬክት ኤነርጂ( Direct Energy) የሚል ተመዝግቦ ያያሉ፤ በካምብሪጅ የማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) የክፍያ ዋጋ መጠን መሰረትም ክፍያዎ ምን ያህል እንደሆነ በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) እንደሚተመን በክፍያ ወረቀትዎ ላይ ተጽፎ ያገኙታል።

**አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች የሚደረግ የአቅርቦት መጠንና የነዳጅ እገዛ ለማግኘት ብቁ ሆነው ተገኝተው ከነበሩ፡ አነኝያኑ ጠቀሜታዎችን ማግኘትዎን ይቀጥላሉ። በዛው ሲደረግሎት በቆየው የአገዛ መጠን ይቀጥላሉ።**

**ላለመሳተፍ መምረጥ፡** ኤቨርሶርስ(Eversource) የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ መሆኑን ይቀጥላል። በክፍያ ሂሳቦ ላይ ያለው የአቅራቢ ክፍያ በኤቨርሶርስ (Eversource) መስረታዊ የዋጋ አገልግሎት (Eversource's Basic Service) መሰረት መታሰቡን ይቀጥላል።

### የመሳተፍ ጠቀሜታ

**የአካባቢ፣ የሚታደስ ኤሌክትሪክ** - ከተማው፤ ከካምብሪጅ የማህበረሰብ ኤነርጂ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program)ተሳታፊዎች የተሰበሰበውን ገንዘብ በመጠቀም የሚታደስ አዲስ ኤነርጂ በመስመሮቹ ላይ ይጨምራል። ከከተማይቱ አዲስ የሶላር ኤነርጂ (solar energy)ፕሮጄክት የሚገኘው አዲስ የሚታደስ ኤነርጂ፤ አረንጓዴ የኤሌክትሪክ (green electricity) ሃይል በማመንጨት በሲ-ሲ-ኢ (CCE) ደንበኞች የኤሌክትሪክ አቅርቦት ላይ የጋዝ አቅርቦት ክፍያ እንዲቀንስ ያደርጋል።

**ምርጫ** - ፕሮግራሙ ሁለት አማራጮችን ይሰጦታል፡1) መደበኛ አረንጓዴ (Standard Green)፤ ይህም ከአዲሱ የካምብሪጅ የሶላር ኤነርጂ (ሃይል) የተገኘውን የሚታደስ ኤነርጂ (renewable energy) በመስመሮቹ ላይ መጨመርን 2) 100% አረንጓዴ ፕላስ (Green *PLUS* )፤ ከ100% የሚታደስ ኤሌክትሪክ እና በመስመሮቹ ላይ ከካምብሪጅ አዲስ የሶላር ኤነርጂ (solar project) ፕሮጀክት የተገኘ የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል መጨመር። **እርሶ በኦቶማቲክ መንገድ በመደበኛው አረንጓዴ ( Standard Green) ይገባሉ። ግን ወደ 100% ግሪን ፕላስ (Green *PLUS*) ለመግባት መምረጥ ይችላሉ። (ስለዚህ ጉዳይ ዝርዝር ከበስተጀርባ ይመልከቱ)**

**ሊሆን የሚችል የገንዘብ ቁጠባ (Potential savings)** - የዚህ ፕሮግራም የክፍያ መጠን ኤቨርሶርስ (Eversource) በመደበኛ የክፍያ አገልግሎቱ ከሚያስከፍለው ዝቅ ያለ ሊሆን ይችላል። ይሁንና የኤቨርሶርስ (Eversource) መደበኛ የክፍያ አገልግሎት፤ በየስድስት ወሩ ለመኖርያ ቤቶችና አነስተኛ የንግድ ቤቶች፤ በየሶስት ወሩ ደግሞ ለትላልቅ የንግድ ቤቶች ደንበኞቹ የዋጋ ለውጥ (prices change) ያደርጋል። በመሆኑም፤ የፕሮግራሙ አከፋፈል ሁሌም ኤቨርሶርስ (Eversource) ከሚያስከፍለው በታች ይሆናል ለማለት አይቻልም፤ የገንዘብ ቁጠባ ይኖራል የሚል ዋስትናም ሊሰጥ አይቻልም።

---

## የካምብሪጅ ማህበረሰብ የ ኤሌክትሪክ ፕሮግራም

(Cambridge Community Electricity Program)

አዲሱ የሙብራት አገልግሎት ክፍያ

**10.20 ¢/kWh**

የኤቨርሶርስ (Eversource) የመኖርያ ቤቶች መደበኛ አገልግሎት

**16.078 ¢/kWh**

የኤቨርሶርስ (Eversource) የአገልግሎት ዋጋዎች ከበስተጀርባ ይገኛሉ። ▶

---

## የደንበኛ እገዛ:

**1-844-379-9934**

### መሳተፍ አይፈልጉም?

**መሳተፍ ካልፈለጉ፡ ግዴታ የለቦትም ፤ ከፕሮግራሙ ለመውጣት የሚከፍሉት መቀጮ ወይም ገንዘብ የለም፡ ባፈለጉበት ግዜ ከፕሮግራሙ ሊወጡ ይችላሉ።**

ላለመሳተፍ ከመረጡ፡ በኤቨርሶርስ(Eversource) መሰረታዊ አገልግሎት ደንበኛ ሆነው ይቀጥላሉ።

በኦቶማቲክ መንገድ ከሚደረግ ምዝገባ ለመዳን፤ በፕሮግራሙ ውስጥ ከመመዝገብዎ በፊት ለመውጣት ሲፈልጉ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን **ከመስከረም (September) 26 ቀን 2023** በፊት ያድርጉ፤

- ▶ ተያይዞ የተላከሎትን ካርድ ይፈርሙና (ፖስታ ቤት የገባበት ቀን **ከ መስከረም (September) 26 ቀን 2023** በፊት መሆኑን የሚያሳይ ጽሁፍ ያለበት ይላኩ። ወይም ወደ ደንበኞች አገልግሎት ክፍል በስልክ ቁጥር **1-844-379-9934** ይደውሉ ወይም ወደ **masspowerchoice.com/Cambridge** ኦንላይን ገብተው ኢሜል ያድረጉ።

ወደፊት ለመውጣት ከፈለጉ ከሚከተለው ውስጥ አንዱን ያድረጉ፡

- ▶ ወደ ደንበኞች መስመር በስልክ ቁጥር **1-844-379-9934** በመደውል ወይም በኦንላይን **masspowerchoice.com/ cambridge** በመግባት ሊወጡ ይችላሉ፤

## የፕሮግራሙ አማራጮችና ዋጋዎች

የማሳቹሴትስ የጋራ ሃብት (Commonwealth of Massachusetts)፤ በ2023 ሁሉም የኤሌክትሪክ አቅርቦት ተቋሞች፤ ቢያንስ 59.2% የሚሆን የኤሌክትሪክ ሃይላቸውን ከሚታደስ ኤነርጂ (renewable energy) እንዲጨምሩ ይጠይቃል። መደበኛ ግሪን (Standard Green) እና 100% አረንጓዴ ፕላስ (100% Green *PLUS*) ሁለቱም ከሚጠየቀው በላይ ናቸው)።

| | | |
|---|---|---|
| **1. ምንም ካላደረጉ፡ በስታንዳርድ ግሪን (STANDARD GREEN) ይገባሉ፤** | | **10.20 ¢/kWh*** ለመኖርያ ቤቶች፣ ለትናንሽና ትላልቅ ንግድ ቤቶች |
| **የሚታደስ የኤሌለክትሪክ ሃይል ይዘት** | **ይህ ማሳሹሴትስ የሚጠይቀውን አነስተኛ የሚታደስ ኤነርጂ (ሃይል) የሚያሟላ ነው። ከአዲሱ የካምብሪጅ የሶላር ፕሮጀክት (Cambridge solar project) ተጨማሪ የሚታደስ ኤነርጂ የሚያቀርብ ነው። **** | |
| **የዋጋ ግዜ (Price period)** | ምዝገባ- ጥር 2024 ሜትር ይነበባል | |
| **የሚያልቅበት ግዜ** | በማንኛውም ግዜ መውጣት ይችላሉ፡ የመውጣት ክፍያ የለም | |

| | | |
|---|---|---|
| **2. ሙቶ በሙቶ (100%) የሚታደስ ኤነርጂ (renewable energy) ከፈለጉ 100% አረንጓዴ ፕላስ (GREEN *PLUS*) ይምረጡ።** | | **13.669 ¢/kWh*** ለመኖርያ ቤቶች፣ ለትናንሽና ለትላልቅ ንግድ ቤቶች |
| ▶ **100% አረንጓዴ ፕላስ (GREEN *PLUS*) ለመምረጥ ወደ ደንበኞች እርዳታ ክፍል በስልክ ቁጥር 1-844-379-9934 ይደውሉ።** | | |
| **የሚታደስ የኤሌለክትሪክ ሃይል ይዘት** | **100% ንጹህ ኤነርጂ (clean energy) ከ ኑው ኢንግላንድ (New England) (ማሳሹሴትስ ክፍል MA Class I RECs) ከሚገኘው የሚታደሱ የኤነርጂ ፕሮጀክቶች ክፍያ (premium) የተገኘ ነው፤ ተጨማሪ የሚታደስ ኤነርጂ ደግሞ ከአዲሱ የካምብሪጅ የሶላር ፕሮጀክት (Cambridge solar project) የቀረበ ነው። **** | |
| **የዋጋ ግዜ (Price period)** | ምዝገባ - ጥር ወር 2024 መለኪያ የተነበበት ወቅት | |
| **የሚያልቅበት ግዜ** | ባፈለጉበት ግዜ መውጣት ይችላሉ፡ ለመውጣት የሚከፍሉት ገንዘብ የለም። | |

| | | |
|---|---|---|
| **3. ለመካፈል ካልፈለጉ በኤቨርሶርስ መሰረታዊ አገልግሎት (EVERSOURCE BASIC SERVICE) ውስጥ ይቆያሉ።** | | **16.078 ¢/kWh** መኖርያ ቤቶች<br>**15.899 ¢/kWh** አነስተኛ የንግድ ቤቶች<br>**15.428 ¢/kWh** ትላልቅ የንግድ ቦታዎች |
| **የሚታደስ የኤሌለክትሪክ ሃይል ይዘት** | ይህ የሚታደስ የኤሌክትሪክ/ሙብራት ሃይል ጥያቄን የማሳሹሴትስ ክፍለሃገር የሚጠይቀውን አንስተኛውን ዋጋ ያሙዋላል። | |
| **የዋጋ ግዜ (Price period)** | ከ ሃምሌ (July) 1 ቀን 2023 እስከ ታህሳስ (December) 31 ቀን 2023 የመኖርያ ቤቶችና ትናንሽ የንግድ ቤቶች ክፍያ፤ ከነሃሴ ( July) 1 ቀን 2023 እስከ መስከረም ( September) 30 ቀን 2023 የትላልቅ ንግድ ቤቶች ክፍያ ይቀየራል፡፡ የኤቨርሶርስ ( Eversource) መደበኛ የአገልግሎት ክፍያ ለመኖርያ ቤቶችና ትናንሽ ንግድ ቤቶች በየስድስት ወሩ ይቀየራል፡፡ ለትላልቅ ንግድ ቤቶች ደግሞ በየሶስት ወሩ ይቀየራል፡፡ | |
| **የሚያልቅበት ግዜ** | በማንኛውም ግዜ ፕሮግራሙን ለቀው ለመውጣት ይችላሉ። የሚከፈል የመውጣት ክፍያ የለም። ይሁንና በተወሰነ የአከፋፈል ምደባ (fixed-price) አገልግሎት ስር የሚገኙ የ ሲ & አይ (የጂ-3 (G-3)፣ የቲ-2 (T-2) እና የደብሊው-አር (WR) ክፍያዎችና የመንገድ ሙብራት ደንበኞች፤ የክፍያ መስተካከል፤ የክሬዲት ወይም የክፍያ ወረቀት ሊደርሳቸው ይችላል። | |

* የስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) ዋጋ እና 100% የግሪን ፕላስ (Green *PLUS*) ዋጋ ሁለቱም ለአንድ ኪሎዋት (kWh) $0.00075 ያስከፍላሉ። የአስተዳደር ክፍያ እና ለአንድ ኪሎዋት (kWh) የ $0.002 የስራ ማካሄጃ ክፍያ አላቸው። የኤሌክትሪክ ማቀበል ስምምነት በሚደረግበት ግዜ የተደረሰ ደግሞ የፕሮግራሙ ዋጋዎች፤ በህጉ ላይ ቀጥታዊ የቁሳቁስ ዋጋ ከፍ የማለት/ለውጥ ከተደረገ፤ ሊጨምሩ ይችላሉ።

** ከአሰራር ውጤት የተሰበሰበው ጭማሪ ገንዘብ፤ አዲስ የሶላር ኤነርጂ ፕሮጀክት በመመስረት በኩል ኢንቨስት ሆኗል። ከተማው፤ ከዚህ ከተሰበሰበው ገንዘብ በስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) እና የ100% ግሪን ፕላስ (100% Green *PLUS*) የሚጠቀሙ የተሳታፊዎችን የኤሌክትሪክ ጠቀሜታ ላይ በከፊል ይውላል።

## በብዛት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**በዚህ ገንዘብ የመቆጠብ ዋስትና አለን?** የለም፡፡ ያሎት ሂሳብ ምን ዓይነት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የኤቨርሶርስ (Eversource) የተተመነ ዋጋ በየስድስት ወሩ ወይም ከዛ ባነሰ ግዜ ውስጥ ይቀየራል፡፡ የመጪ ግዜ ዋጋም ምን ያህል እንደሚሆን የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ የኤቨርሶርስ (Eversource) ለመኖርያ ቤቶችና ለትናንሽ ንግድ ቤቶች የተተመነ መሰረታዊ ዋጋ ጥር (January) 1 ቀን 2024 ይቀየራል፡፡ የትላልቅ ንግድ ቤቶች ዋጋ ደግሞ ጥቅምት (October) 1 ቀን 2023 ይቀየራል፡፡ ወቅታዊ ዋጋዎች ምን እንደሆኑ ለማወቅ በኦንላይን ወደ https://www.eversource.com. ገብተው ይጎብኙ፡፡

**ከአንድ የሃይል አቀባይ ተቋም ጋር ውል ተፈራሜአለሁ፤ ምን ማድረግ አለብኝ?** ከአንድ የኤሌክትሪክ ሃይል አቀባይ ጋር ውል ካሎትና ከዚሁ አቀባይ ጋር ባደርጉት ውል መቆየት ከፈለጉ፤ ከዚህ ከካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) መውጣት አለቦት። ከፕሮግራሙ ለመውጣት የሚወሰዱትን እርምጃዎች ካልወሰዱና ካልወጡ፤ በኦቶማቲክ መንገድ ይመዘገባሉ፤ ከዛም በላይ ከኤሌክትሪክ አቀባዮ ቅጣት ሊያስከትልቦት ይችላል።

**ከግብር ነጻ የሆነ አካውንት ነው ያለኝ፤ ይህንን ያለኝን ከግብር ነጻ የሆነ ሂሳቤን እንዴት ነው መጠበቅ የምችለው?** እንደ አንድ የፕሮግራሙ የኤሌክትሪክ አቅርቦት የክፍያ አካል መጠን፤ የሚከፍሉት ግብር ይመደብሎታል። ከግብር መክፈል ነጻ የሆኑ ደንበኞች፤ ተገቢ የሆኑ ከግብር ነጻ መሆንዎን የሚያመለክቱ ዶኩመንቶችን መለየትና ወደ ዳይሬክት ኤነርጂ (Direct Energy) ማቅረብ የእነሱ ሃላፊነት ነው። ዶኩመንቶችዎን የት እንደሚያቀርቡ መረጃ ለማግኘት ወደ masspowerchoice.com/cambridge ገብተው ይጎብኙ።

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካልዎት፣ እባክዎን ከደንበኞች እገዛ ክፍል አባሎች (customer support) ጋር በ **1-844-379-9934** ደውለው ይገናኙ ወይም ወደ **cambridge@masspowerchoice.com** ይጻፉ፣ ወይም በኢንተርኔት ወደ **www.masspowerchoice.com/cambridge** ይግቡ። የፕሮግራማችን አማካሪዎች እርስዎን ለመርዳት ደስተኞች ይሆናሉ፡፡ ወይም ደግሞ የካምብሪጅ ከተማን በቀጥታ በ 617-349-5323 ማግኘት ይችላሉ።

ይ-አን ሁዋንግ (Yi-An Huang)
የከተማ አስተዳዳሪ (City Manager)

# የመውጫ መመለሻ ካርድ

## የካምብሪጅ ማህበረሰብ ኤሌክትሪክ ፕሮግራም

X ______________________________________________

ፊርማ ቀን

## የመውጫ መመርያዎች

በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ ከፈለጉ ምንም አይነት እርምጃዎችን መውሰድ አይኖርቦትም።

**በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ካልፈለጉ፤ መውጣት አለቦት።** የሚወጡት መንገድ ፖስታ በመላክ ከሆነ፡

1. **በዚህ ካርድ ላይ ቀኑን ጽፈው ይፈርሙ**
2. **ካርዱን በተካተተው ፖስታ ውስጥ ያሽጉ**
3. **ፖስታውን በፖስታ ቤት በኩል ይላኩ**

ይህ ካርድ፤ ስሙ ከላይ በተጻፈው በመዝገብ ቤት ሹም መፈረም አለበት። ከአቶማቲክ ምዝገባ ለመዳን፤ ካርዱ ፖስታ ቤት የገባው **ከመስከረም (September) 26 ቀን 2023** በፊት መሆኑን የሚያሳይ መሆን አለበት። ባፈለጉት ግዜ ከፕሮግራሙ ለመወጣት ይችላሉ፣ ይህም ወደ **masspowerchoice.com/cambridge** በመግባት ወይም ወደ ደንበኞች አገልግሎት በስልክ ቁጥር **1-844-379-9934** በመደወል ሊፈጸም ይችላል።